# የፍልሰታ ጾም የተመረጡ ምስባኮች

# ዘሠርክ ምስባክ - ነሀሴ ၊

## አፅምእ እግዚኦ ጸሎትየ።
## ወነጽር ,ቃለ ስእለትየ።
## በዕለተ ምንዳቤየ ጸራኀኩ ኀቤከ እስመ ሰማዕከኒ።

መዝ. 95 6 - 7

አቤቱ ጸሎቴን አድምጥ።
የልመናዬንም ድምፅ ስማ።
ትመልስልኛለህና በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጠራለሁ።

# ዘሠርከ ምስባክ - ነሀሴ 2

## ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ።
## ወይበዝኅ ከመ ዘግባ ዘሊባኖስ።
## ትኩላን እሙንቱ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር።

መዝ. 91 12 - 13

ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፥
እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል።
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል።

# ዘሠርክ ምስባክ - ነሀሴ 3

## እስመ ይትዌደስ ኃጥእ በፍትወተ ነፍሱ።
## ወዐማፂኒ ይትባረክ።
## ወሀኮ ኃጥእ ለእግዚአብሔር።

መዝ. 9 23 – 24

ኃጢአተኛ ወዶ በሰራው ይወደሳልና
ዓመፀኛም ይመሰገናል።
ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን አወከው።

# ዘሠርከ ምስባክ - ነሀሴ 4

## ወእለሂ ይኤብሱ ኢያንሥኡ ቀርኖሙ። ወኢያንሥኡ ቀርኖሙ ውስተ አርያም። ወኢይንብቡ ዐመፃ ላዕለ እግዚአብሔር

መዝ. 74 4 - 5

የሚበድሉም ሀይላቸውን አያንሱ፤
ሀይላቸውን ወደ አርያም አያንሱ፥
በእግዚአብሔርም ላይም ዓመፅን አይናገሩ።

## ዘሠርክ ምስባክ - ነሀሴ 5

# ወተሐሥያ አዋልደ ይሁዳ።
# በእንተ ፍትሕከ እግዚኦ።
# እስመ አንተ እግዚአብሔር ባህቲትከ ልዑል ዲበ ኵሉ ምድር ።

መዝ. 96 8 - 9

አይሁዳ ልጃገረዶችም ደስ አላቸው፥
አቤቱ ስለ ፍርድህ።
አንተ እግዚአብሔር ብቻህን በምድር ላይ ከፍ ያልክ ነህና።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 6

## ጐሥዐ ልብየ ቃለ ሰናየ።
## ወአነ አይድዕ ግብርየ ለንጉሥ።
## ከመ ቀለመ ፀሀፊ ዘጠበጠበ ይጽሕፍ ልሳንየ።

መዝ. 44 1-2

ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ፤
እኔ ስራዬን ለንጉሥ እነግራለሁ።
አንደበቴ እንደ ፈጣን ጸሓፊ ብርዕ ነው።

# ምስባክ - ነሐሴ 7

ብፁዕ ብእሲ ዘአንተ ገሠጽኮ እግዚኦ።
ወዘመርሀኮ ሕግከ።
ከመ ይትገኃሥ እመዋዕለ እኩያት።

መዝ. 93 12-13

ብፁዕ ነው እግዚአብሔር ሆይ አንተ የምትገሥጻው፣
ከሕግህም የምታስተምረው ሰው፤
ለኀጢአተኞች ጕድጓድ እስኪማስላቸው ድረስ፣

# ዘሰርከ ምስባክ - ነሐሴ 7

ሕፅበኒ ወአንጽሐኒ አምኃጥያትየ።
ወእምአበሳየኒ አንጽሐኒ።
እስነ ለልየ አአምር ጌጋይየ።

መዝ. 50 2-3

ከበደሌ ፈፅሞ እጠበኝ።
ከኃጢአቴም አንጻኝ።
እኔ መተላለፌን አውቃለሁና።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 8

## ዘረወ ወወሀበ ለነዳይ።
## ወጽድቁኒ ይነብር ለዓለም።
## ወይትሌዐል ቀርኑ በክብር።

መዝ. 111 8-9

በተነ ለችግረኞችም ሰጠ።
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል።
ክብሩ በክብር ከፍ ከፍ ይላል።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 9

ይረትዕሰ ይርታዕ ፍኖትየ።
ከመ እዕቀብ ኵነኔከ።
ውእተ ጊዜ ኢይትኀፈር።

መዝ. 118 4-5

ትእዛዛትህን እጅግ እንጠብቅ ዘንድ አንተ አዘዝህ።
ሥርዓትህን ለመጠበቅ።
መንገዶቼ ይቀኑ ዘንድ እወድድ ነበር።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 10

ወይስተጋብእ ዝርዎቶሙ ለእስራኤል።
ዘየፌውሶሙ ለቀኍስላነ ልብ።
ወያፀምም ሎሙ ቀኍስሎሙ።

መዝ. 147 2-3

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይሠራል።
ከእስራኤልም የተበተኑትን ይሰበስባል።
ልባቸው የቈሰሉትን ይፈውሳል።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ ፲፩

ኀይሎሙ ውእቱ እግዚአብሔር ለእለ ይፈርህዎ።
ወስሞሂ ለእግዚአብሔር ለእለ ይጼውዕዎ።
ወሕጎሂ ይሜህሮሙ።

መዝ. 24 14-15

እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው።
ቃል ኪዳኑንም ያስታውቃቸዋል።
እርሱ እግሮቼን ከወጥመድ ያወጣቸዋልና።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 12

## ተዐውቀ በላዕሌነ ብርሀነ ገጽከ እግዚኦ።
## ወወደይከ ትፍሥሕተ ውስተ ልብነ።
## እምፍሬ ስርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኀ።

መዝ. 4 6-7

በጎውን ማን ያሳነይናል የሚሉ ንዙ ናቸው።

አቤቱ የፊትህ ብርሃን በላያችን ታወቀ።

በልቤ ደስታን ጨመርህ ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ።

# ዘነግህ ምስባክ - ነሐሴ 13

ደብር ርጉዕ ወደብር ጥሉል።
ለምንት ይትነሥኡ አድባር ርጉዓን።
ደብር ዘሠምሮ እግዚአብሔር የኀድር ውስቴቱ።

መዝ. 67 15-16

የጸና ተራራና የለመለመ ተራራ ነው።
የጸኑ ተራራዎች ለምን ይነሣሉ?
እግዚአብሔር ይህን ተራራ ያድርበት ዘንድ ወደደው፤

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 13

ፈነወ እግዚአብሔር ሣህሎ ወጽድቆ።
ወአድኅና ለነፍስየ እማእከለ አናብስት።
ወኖምኩ ድንጉፀየ።

መዝ. 56 3-4

ከሰማይ ልኮ አዳነኝ።
ለረገጡኝም ውርደትን ሰጣቸው።
እግዚአብሔር ቸርነቱና እውነቱን ላካ።

# ምስባክ - ነሐሴ 13

ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ።

ወይሴብሑ ለስምከ።

መዝራዕትከ ምስለ ኃያል።

መዝ. 88 12-13

ታቦርና አርሞንዔም በስምህ ደስ ይላቸዋል።

ክንድህ ከኃይልህ ጋር ነው፤

እጅህ በረታች ቀኝህም ከፍ ከፍ አለች።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 14

ወእሙን ኵሉ ትእዛዙ።
ወጽኑዕ ለዓለመ ዓለም።
ወግቡር ለጽድቅ ወበርትዕ።

መዝ. 110 8-9

ለዘላለምም የጸና ነው።
በእውነትንና በቅንም የተሠራ ነው።
መድኃኒትንም ለሕዝሁ ሰደደ ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 15

እብን ዘመነንዋ ነድቅት።
ወይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማእዘንት።
እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ።

መዝ. 117 22-23

ግንበኞች የናቁት ድንጋይ።
እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ።
ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች።

# ዘነግህ ምስባክ - ነሐሴ 16

ወትቀውም ንግሥተ በየማንከ።
በአክባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኁኲብርት።
ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ እዝነኪ።

መዝ. 44 9-10

የንጉሦች ሴት ልጆች ለክብርህ ናቸው።
በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግስቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።
ልጄ ሆይ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ።

# ዘሰርክ ምስባክ - ነሐሴ 16

እስመ ለእግዚአሔር መንግስት።
ወውእቱ ይኴንኖሙ ለአሕዛብ።
ብልዑ ወስግዱ ኲልክሙ ጥሉላነ ምድር።

መዝ. 21 28-29

መንግስት ለእግዚአብሔር ነውና።
እርሱም አሕዛብን ይገዛል።
የምድር ደንዳኖች ሁሉ ይበባሉ ይሰግዳሉም።

# ምስባክ - ነሐሴ 16

ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል።
እግዚአብሔር ውስተ ማዕከላ ኢትትሀወክ።
ወይረድኣ እግዚአብሔር ፍጽመ።

መዝ. 45 4-5

ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ።
እግዚአሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም፥
እግዚአብሔርም ፈጥኖ ይረዳታል።

# ዓዲ ምስባክ - ነሐሴ 16

ወተዚያነዉ ዳኅናሃ ለኢየሩሳሌም።
ወፍሥሓሆሙ ለእለ ያፈቅሩ ስመከ።
ይኩን ሰላም በኃይልከ።

መዝ. 121 6-7

ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ፤
አንተንም ለሚወድዱ ልማት ይሁን።
በኃይልህ ሰላም ይሁን፥

አዘጋጅ፡የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስትያን ሞንትሪያል፤ ካናዳ

**Prepared By: Ethiopian Orthodox Tewahedo Medhane-Alem Church of Montreal Canada።**